PANORAMA # XXXVI

## የትዝብት አድማስ

ነሀሴ 1 ቀን 2000 ዓም

## የተስፋ ዳቦ ማስገመጥ ረሀብን አይከላም

*አምባገነን መሪዎች የሚገዙትን ሕዝብ ሥነልቦና ለመስለብ፥ አዕምሮ ለማጠብና በቅሎ ወለደች ብሎ ለማሳመን የማይበጥሱት ቅጠል አይገኝም:: ሁለንተናዊ ፕሮፓጋንዳ እያካሄዱ የሕዝብን አቅጣጫ ለማስቀየር መመከር የሥልጣን ዘመናቸውን የሚያስረዝምላቸው ስለሚመስላቸው ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ:: የተራቀቀ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በማድረግ የተዋጣለት አምባገነን ሥርዓት የናዚ ጀርመን እንደነበረ ተደጋግሞ ይጠቀሳል:: በተለይ የፕሮፓጋንዳውን ኃላፊነት የተረከበው ጆሴፍ ጉብልስ የተባለው ግለሰብ የምልዓተ- ሕዝቡን አዕምሮ ለመስለብ ልዩ ተሰጦ እንደነበረው ታሪክ ፀሀፊዎች ያወሱለታል:: ፕሮፓጋንዳ፥ በድርጊት ካልተደገፈ፥ የባዶ በርሜል ጩኸት ይሆናል ብለው ያምኑ ስለነበር፤ ሂትለርና ግብረ አበሮቹ በአስራ ሁለት ዓመታት የሥልጣን ቆይታቸው፥ ጀርመንን ከወደቀችበት የአንደኛው የዓለም ጦርነት ውርደትና ጥቃት አንስተው የአውሮፓ ኃያል ሀገር እንዳደረጓት ጠላቶቻቸው ሁሉ ሳይቀሩ መስክረውላቸዋል:: ጀርመንን መገንባት ከፕሮፓጋንዳቸው ጋር አዛምደው ናዚዎቹ እንደተጠቀሙበት በጊዜው የነበረው የጀርመን ዜጎች አምነውበት ነበር ቢባል ስህተት አይመስልም:: ያም ሆኖ ግን ፕሮፓጋንዳቸው ከመጨረሻው ውድቀታቸው ሊያድናቸው አልቻለም:: የፈፀሙትንም አረመኒያዊ ወንጀል ሊሸፍንላቸው ከቶ አልቻለም:: በመሆኑም በጨረሻው ሰዓት፥ ከፍርድ ሸንጎም ይሁን ከታሪክ ፊት ለማምለጥ አልሆነላቸውም::*

*የወያኔ መሪዎችም እንደ አቅሚቲ ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማታለል መፍጨርጨር ከጀመሩ ይኸው አስራ ሰባት ዓመታትን አስቆጥረዋል:: በእነኝህ ተፈራራቂ ዓመታት፥መስከረም በጠባ ፥ ህዳር በታጠነ፥ መባቻ/ልደታ ባባተ ቁጥር፥አዳዲስ ውሸትና ቅጥፈት እያመጡ ምልዓተ ሕዝቡን ለማወናበድ መቻል የሥልጣን ዘመናቸውን የሚቀጥልላቸው ይመስላቸዋል:: በተለይ መለስ ዜናዊማ ቆርጠ በመቀጠል የውሸት ችሎታው የተካነበት መሆኑን በተደጋጋሚ አስመስክሯል:: ምናልባት ወደ ፊት ልክ እንደ ኦሎምፒክስና እንደ ዓለም ዋንጫ ውድድር፥ የውሸታሞች ውድድር ቢዘጋጅ፥ ኢትዮጵያ ሀገራችን እነ መለስ ዜናዊን በውድድር አሰልፋ የወርቅ ዋንጫ እንደምታገኝ ጥርጥር አይኖርም:: የውሸት ንግግር እያሰሙ፥ በቀቢፀ-ተስፋ ኑሮ እያስኖሩና የተስፋ ዳቦ እያስገመጡ ሕዝብን ለዘለዓለም መግዛት እንደማይቻል ግን አልተረዱትም:: መለስ ዜናዊ በቅርቡ የላስቲክ ማኅተም ለሆነው የወያኔ*

ፓርላማ በአቀረበው የሥራ ዘገባ፥ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ፥ 7-8 ከመቶ እንዳደገ፤ የእህል ምርቱ እንደተመነደገ፥ የሥራ አጡ ቁጥር እንደተቀነሰ፥ የትምህርትና የጤና አገልግሎቶች እንደተጥለቀለቁ፥ የምዕዋተኛውና የጎዳና ተዳዳሪው መጠን እንደተወገደ፥ ፍትኀ-ርትዕ እንደሰፈነ፥ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች እንደተከበሩ ዲስኩሩን ደስኩሯል። የልማቱ ዕድገት እንደተጧጧፈም የሲ.ቃ ምፀት በተላበሰ ቅጥፈት ተናግሮ፥ የአሽቃባጮቹን ጭብጨባ ለማግኘት ጥሯል። ከንግግሩ በኋላም መለስ አጨብጫቢዎቹን ዘገባውን እንዲያፀድቁለት ጠይቆ የጠየቀውን አድርገውለታል። ስለውሸት ዘገባው ግን በብዙዎቹ የምክር ቤት አባላት አለመጠየቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያው እንደተለመደው በትዝብት አልፎታል። ትዝብት አይፈሬው መለስም እያሾፈ ወደ ቤቱ ሄዷል።

ከፕሮፓጋንዳውና ከውሸት ዲስኩሩ ባሻገር ግን የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ አልተለወጠም። የኢትዮጵያ ነባራዊ ሀቅ የሚያሳየውም ተቃራኒውን እንደሆነ ማንም ሊያስተባብለው አይችልም። ምኞትና ባዶ ተስፋ ደግሞ ከንቱ ነባቢት እንጅ፥ የሕዝቡን የመከራ ኑሮ ገፅታ የተሻለ እንዲሆን አያደርገውም። "ደሀ በጎልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኖሮ እከክ ይጨርሰው ነበር" ብሎ ለማፌዝ ካልሆነ በስተቀር፥ የነመለስ ፕሮፓጋንዳ ለተራበው ዳቦ፥ ለተጠማው ውሃ ለታረዘው ልብስ ሊያመጣለት አይችልም። ኢኮኖሚው ከዕለት ወደ ዕለት እለት እያሽቆለቆለ መሄዱን የዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት እየመሰከሩ እያሉ፥ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ ምጣኔ ኃብት 7 በመቶ አድጓል ሲል በጠራራ ፀሀይ ይዋሻል። መዋሸቱ ብቻ ሳይሆን፥ ዓለምንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማታለል ድፍረት ማግኘቱ የሚያስደንቅ ነው።:: "የሌባ ዓይነ-ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ" ይሏል ይህ ነው። መለስ ዜናዊ በዚህ ጓደኛው የፓርላማ ዘገባው ውስጥ ሀገሪቱ በሁለንተናዊ ገፅታዋ እያደገች እየተመነደገች፥ ሕዝቧም እየበለፀገ፥ በልማት ጎዳናም እየተራመደ፥ እየገሰገሰ እንደሆነ ዓይኑን በጨው ሳያጥብ ቢዋሽም፥ ይህንን የውሸት አሀዝም ሆነ ስታትስቲክስ ግን እንዴት እንዳገኘው ማገናዘቢያና ምንጭ ሊጠቅስ አልቻለም። ሪፖርቱን አዘጋጅተው የሰጡት አገልጋዮቹም፥ እራሳቸውን ደልለው፤ መለስን አታልለው፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ በማጭበርበራቸው፥ ታላቅ ብሔራዊ ክህደት መፈፀማቸውን የሚገነዘቡት አይመስልም። ምን ጊዜም ቢሆን፥ በአምባገነን ሥርዓት ዙሪያ የሚኮለኮሉ፡ አገልጋዮችና እበላ ባዮች ኅሊናቸውን የሸጡ፥ ሰብዕናቸውን የዳረጉ፥ አዕምሯቸውንም የከዱ በመሆናቸው፤ ዕውነቱን ለመናገር ድፍረቱም፥ ችሎታውም አይኖራቸውም። ሰብዕናቸው ጠቅላላ በፍርሀትና በእበላባይነት የተመሰጠ በመሆኑ፥ የሀገሪቱን ዕውነተኛ ገፅታ፥ የሕዝቡንም ዕሮሮ ለመግለፅ የሚሳሳ አንጀትና የድፍረት ሀሞት የላቸውም። ይህ ዓይነቱ ክስተት በሀገራችን በተፈራረቁት አምባገነን ሥርዓቶች የተደጋገመ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል። እስካሁን ግን እየታዘበ፥ አንጀቱ እያረረና የተሻለ ዘመን እንዲመጣ ከመመኘት በስተቀር ምንም ሊያደርግ አልሆነለትም። መፍትሄውን ግን በዳግማዊ የካቲት ሕዝባዊ አመፅ እንደሚያገኝ አይጠራጠርም።

በአፄው ሥርዓት፥ አስተዳደሩ እየተበላሸ፥ የሕዝቡ ሰቆቃ እየተባበሰ፥ ፍትኅ-ርትዕ እየተረገጠ፥ ሀገሪቱ የረኃብ፥ የበሽታና የድኅነት ሰላባ እየሆነች፥ እያዩና እየሰሙ፥ የአፄው የቅርብ አማካሪዎች ሀገሪቱ እንዳደገች፥ ሕዝቡም እንደበለፀገ፥ እንደተደሰተም አድርገው ይነግሯቸው ነበር ይባላል። እራሳቸው ንጉሡንም የኢትዮጵያ መሲኅ፥ የአፍሪካ ጮራ፥ የዓለም ብርኃን ናቸው እያሉ በከንቱ ወዳሴ ያቆለጳጵሷቸው እንደነበር ያ ትውልድ የሚያውቀው ነበር። ምናልባት በጣት የሚቆጠሩ አንዳንድ የሕዝብ ታማኞችና የሀገር ተቆርቋሪዎች የሀገሪቱን ጠቅላላ ችግር ለማስረዳት ቢሞክሩም፥ ሰሚ ሳያገኙ ቀርተዋል። አንዳንዶቹም ለወኅኒ ተዳርገዋል። የ66ቱ ዐብዮት መጥቶ እስከገላገለው ድረስ፥ ያ ሥርዓት  እራሱን እያታለለ የሚኖር ነበር። ደርግም በመፈክር እየዳጨረ፥ በአደባባይ እየደነከረ፥ የሃሰት  ፕሮፓጋንዳውን ከማጠናከር አልፎ ተርፎ፥ የሀገሪቱን ዕውነተኛ ሁኔታም ሆነ የሕዝቡን መከራና ስቃይ የሚያይበት አዕምሮም፥ ዕውቀትም፥ ጊዜም አልነበረውም። በደርግ ዙሪያ ተኮልኩለው የነበሩትም፥ የቅጥፈት መፈክር እንዲያሰማ ከመምከር በስተቀር፥ መንግሥቱ ኃይለማርያምን፥ በዕርሱ ምክንያትና ትዕዛዝ ዕልፍ አዕላፍ ዜጎች ወደ መቃብራቸው እንደወረዱ አንስተው ተው ሊሉት አልደፈሩም። በአያሌ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንም በወኅኒ እንደሚሰቃዩ አንስተው ይፈቱ ሊሉ አልቻሉም፥ አልደፈሩም፥ አልፈለጉምም። ይልቁንም፥ ሀገሪቱ  በዴሞክራሲ መንገድ እንደምትመራ፥በሶሻሊስት ዕድገትና ብልፅግና እንደተኀናፀፈች፥ በመላው ኢትዮጵያም ሰላምና መረጋጋት እንደሰፈነ አድረገው ነበር የሚነግሩት። ተክለ ሰብዕናውንም  በቀቢፀ-ተስፋ እየገነቡ፥ አብዮታዊ መሪያችን፥ የሶሻሊስት ጀግና፥ ቆራጡ ሀገር ወዳድ፥ በማለት የፍርኀት ምስጋና ሲያሽጎደጉዱለት  ነበር። ግብዙና አረመኔው ኮለኔል ደግሞ ወንጀሉንና ግፉን ረስቶት ወይም ጠፍቶት ሳይሆን፥ አላወቅኩም ነበር ማለቱ ያዋጣኛል ብሎ ነው። በመጨራሻ ግን ደርግና ሀገሪቱ መጨረሻቸው ምን  ላይ እንደወደቁ ታሪክ ስለመዘገበው ያንን መዘርዘር አስፈላጊ አይደለም።

ከእነርሱ በፊት እንደነበረው እንደ ደርጉ ሥርዓት ሁሉ፥ የአሁኖቹ የወያኔ ግልገሎችም ተመሳሳይ ፕሮፓጋንዳ በማካሄድ ሀገርንና ሕዝብን በማጥፋትና በመበደል ላይ ይገኛሉ። ሀገሪቱ ዕለት በዕለት ወደ አዘቅት መሄዷ የአደባባይ ምሥጢር መሆኑ እየታወቀ፥ ሰላም፥ ዴሞክራሲና ብልፅግና ሰፍኗል ብለው ለማታለል ይጥራሉ። ኢትዮጵያን ምድራዊ ሲዖል አድርገው እየገዙ፥ ሀገሪቱን አምሳለ-ገነት እንደሆነች አድርገው የውሸት ስዕል ይስላሉ። ባዶ ፕሮፓጋንዳ፥ የውሸት ዲስኩርና የዘወትር ቅሌት የኢትዮጵያን ችግር ይፈታው ይመስል፥ ብሎም፥ ለተራበው ዳቦ፥ ለታረዘው ልብስ፥ ለኀሙማን መዳኀኒት፥ ለኀዳና ተዳዳሪው መጠለያ  ታዛ፥  ወኅኒ ውስጥ ለሚማቅቀው፥ ነፃነት፥ ላዘነው መፅናናት ይሰጥ ይመስል፥ መለስና ግብረ አበሮቹ፥ በሀገራችን ሕዝብ ላይ ምፀት የተመላበት ንቀትና ማሾፍ ይፈፅሙበታል። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና የደርግ መንግሥታት፤ በዕርግጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ረግጠው ገዝተዋል። ይፈሩትም ነበር። ያሰጋቸውም ነበር። ምናልባትም ከፍርኃት የመጣ ጥላቻም አሳይተውም ይሆናል። አምባገነናዊ ፕሮፓጋንዳም አካሂደውበትም ነበር። የወያኔ መሪዎች ግን ከፍርኃት የመጣ ጥላቻ ማሳደራቸው ብቻ ሳይሆን፥

ከራሳቸው የዝቅተኝነት ስሜት በመነሳት የኢትዮጵያን ሕዝብ ንቀውታል። አዋርደውታል። ሰድበውታል። ሰድበውም ለሰዳቢ ዳርገውታል። “በአስራ ስምንት መቶ ሰማኒያ አንድ ( 1881) ዓ.ም ሸዋ የወሰደውን የትግሬን መንግሥት፥ ይኸው እኛ ልክ ከአንድ መቶ ዓመት በኋላ በ1981 ዓ.ም. በእጃችን አስገባነው” እያሉ የሚመፃደቁትም፥ ከጀግንነት፥ ሳይሆን፥ ከበቀል፥ ከጥላቻና ከዝቅተኝነት ስሜት መሆኑን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደኅና አድርጎ ተገንዝቦታል። የኢትዮጵያ ችግር ደግሞ፥ በቂም- በቀል፥ በጥላቻና ሕዝብ እየናቁ በመፍራት አይፈታም። በባዶ ፕርፓጋንዳ ዘመቻም መፍትሄ አይገኝም። የሀገራችን ፈርጀ-ብዙና ወርደ -ሰፊ ችግር የሚፈታው በመከባበር፥ በመተሳሰብ፥ በመተባበርና ሁሉንም ዜጋ በማሳተፍ ብቻ ነው። ይህ ሂደት የሚመጣው ደግሞ ከታላቅነት፥ ከአርቆ ስተዋይነትና ከሀገርና ከሕዝብ ፍቅር ከሚመነጭ ወገንተኝነት ነው። የወያኔ መሪዎች መንፈሰ-ደካማ፥ ናላቸው በጥላቻ የተመላና በሥነ ልቦናም ለዚህ ሀገራዊ ተግባር ስለአልተዘጋጁ፥ አቅሙም ስለ ሌላቸው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ታርቀው ለተሻለ ተግባር ፈቃደኞች ይሆናሉ ተብለው አይጠበቁም። ከዚህ ይልቅ የሃሰት ፕሮፓጋንዳ መንዛቱን ያገዛዛቸው ዓይነተኛ የአሰራር ዘየ አድርገው ይዘውታል። የያዙት መንገድ ግን የዕድሜያቸውን ማጠር ከማብሰሩ በቀር ሌላ ፋይዳ አያስገኝላቸውም። የኃሰት ፕሮፓጋንዳ እንኳንስ ለመለስ ዜናዊ፥ ለናዚዎቹም አልፈየደ። የኢትዮጵያንም ተጨባጭ ሁኔታ አይለውጠውም። ሕዝባችን “ላም አለኝ በሰማይ” ማለትን ካበቃ ብዙ ጊዜ ማለፉን ደግሞ ወያኔ ውደቀቱን በሚያመጣው ትግል እሳት ሲለበለብ የሚረዳው ይሆናል። ጊዜ ካለፈ! ነገር-ዓለሙ ከተበላሸ! ሥልጣኑ ከተገረሰሰ! መቃብሩ ከተማሰ! ከፈኑ ከተቀደደ በኋላ ይሆናል። ያ ወቅት ደግሞ ከፈርስ ላይ ማጓጎር ነው የሚሆነው። የወያኔ መሪዎች፥ “ልመና ሳሉ በቁመና” የሚለውን የሀገራችንን ይትበኃል ደፍሮ የሚነግራቸው አላገኙም። ተነገሩም አልተነገሩም፥ ወያኔዎቹ ለኢትዮጵያ ጥፋት ስለመጡ ለዓላማቸው ይጠቅመናል ብለው የያዙትን የሀሰት ፕሮፓጋንዳቸውን ከመርጨት ወደ ኋላ የሚሉ አይሆኑም። የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ግን በመጨረሻ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣና ፍርድ ቅጣት ሊያድናቸው እንደማይችል የታሪክ ሀቅ ነው።